**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)**
***Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)***

ጥር 14 ቀን 2010 ዓም

# <u>በወልድያ ሠላማዊ  ሕዝብ ላይ የተፈፀመውን ግድያ ኢሕአፓ አጥብቆ ይኮንናል</u>

የጥምቀትን  በዓል ለማክበር በወጣው የወልድያ ሠላማዊ ሕዝብ ላይ፤ የወያኔ ነፍሰ ገዳይ ቡድን የጅምላ ጭፍጨፋ  ፈጽሟል። የበርካታ ሠላማዊ ዜጎች ህይወት ጠፍቷል። ቁጥሩ በውል ያልተመዘገበ ንፁኽ ሕዝብ እንደቆሰለም ከቦታው የተገኙ የዐይን ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡  የገቡበት ያልተወቁትን  የወልድያ ነዋሪዎች ለማግኘት፤ ፍለጋው ቀጥሏል።

ታቦቱን አክብረው ተሸከመው በወጡት ቀሳውስትና ዲያቆናት ላይ  አስለቃሽ ጪስ ስለተተኮሰባቸው፤ ቅዱስ-ክቡር የሆነው ታቦታቸው ተዋርዶ ከመሬት ላይ ወድቋል።  በዚኽ እጅግ አሳዛኝ ተግባር፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ተቆጥቷል።  ወንጀሉንም  አምርሮ አውግዟል።

ይኽ በወልድያ ላይ የተፈጸመው ሀገራዊ ወንጀል የወያኔን ትክክለኛ ምንነትና ባህርይ የበለጠ ገልጾታል። ወያኔ ፤ የሆነው እየሆነ፤ በሥልጣኑ ለመቆየት ማንኛውንም ወንጀልና የጅምላ ጭፍጨፋ ከመፈጸም እንደማይመለስ ፤ በሚገባ  አረጋግጧል።  ወያኔ ስህተት ሠርተናል ከሕዝብ እንታረቃለን ባለ ማግስት ይኽ በወልድያ ላይ የፈፀመው  ወንጀል፤ "ከዕባብ ዕንቁላል  ዕርግብ  እንደማይፈለፈል" በማያጠራጥር መንገድ አሳማኝ ሆኗል። ዘረኛው አገዛዝ የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም፤ ማንኛውንም ወንጀልና ክኅደት ከመፈፀም እንደማያመነታ፤ በተደጋጋሚ አሳይቷል። ሠላማዊ ሕዝብ በጅምላ እየጨፈጨፉ በሥልጣን መቆየት፤ የወያኔ ዐልፋ ኦሜጋ ነው - አራት ነጥብ።  "ወያኔ እየተሻሻለ በመሄድ ላይ ስለሆነ፤ አብሮ መሥራት ይቻላል"  ለሚሉት ሁሉ፤  "ዕርማችሁን አውጡ!"  ሲል ወያኔ በወልድያ ድርጊቱ ዕቅጩን ነግሯቸዋል።

ኢሕአፓ፤ በወልድያ ወገኖቹ ላይ የተፈፀመውን ዐረመኔያዊ የጅምላ ግድያ አጥብቆ ይኮንናል ! ያወግዛል !
መላው  የኢትዮጵያ ሕዝብ  በወያኔ ላይ የሚያካሂደውን ተቃውሞ እንዲቀጥል ጥሪውን ያስተላልፋል !
ሞት ለዘረኛው አገዛዝ !
ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው !

**EPRP**
**P.O.BOX  73337**
**Washington DC,  20056**
**USA**

**Email  ESPIC@aol.com**
**Website  www.eprp.com**

**EPRP**
**BP  30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

Tel.  202 291 4217    Fax:  202 291 7645